# እጅግ አስገራሚው የወያኔ/ኢሕአዴግ አጋንንታዊ
# የግድያ ድራማ ከሰይጣናዊ ዓላማው ጋር ሲጋለጥ!!!

አማራ ሆይ! ቢገባህ ሞተህ የተቀበርከው አሁን ነው!!!

"አለንልህ ከጎንህ ነን!" እያልክ ገፋፍተህ ገፋፍተህ ይሄንን ጀግና አርበኛ ጄኔራል አሳምነው ጽጌን እና ሌሎች ጀግኖች አርበኞች ጓዶቹን አስበልተህ ዝም ብለህ ከተቀመጥክ በቁምህ ሞተህ መቀበርህን ዕወቀው!!! ጀግናውን አሳምነው ጽጌን የምትከዳ አማራ ሰማይ ምድሩ ይክዳህ!!! ጨለማው አይንጋልህ!!! ይህ ጥቃት የተሰነዘረው በአማራ የህልውና ትግል ላይ መሆኑን መገንዘብ የተሳነው አማራ ካለ በቁምህ የሞተ በድን ሬሳ ነው ወይ ደግሞ የወያኔ/ብአዴን ቅጥረኛ ነው!!!

እነ ጌታቸው አሰፋ ተቆርቋሪ፣ ተፈሪ፣ አሳቢ፣ ጠባቂ ወገን ስላላቸው ከዘር ማጥፋት ወንጀል እስከ አረመኔያዊ ሰቆቃ (ቶርቸር) ድረስ የፈጸሙ፣ ወንጀል ከተባለ ሁሉ አንድም ያልፈጸሙት ወንጀል የሌላቸው በዓለማችን ቁጥር አንድ ወንጀለኛ ሆነው እያለ ጫፋቸው ሳይነካ ተንቀባረው በምቾት ይኖራሉ፡፡ እነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌ ግን ለወገናቸው ተቆርቋሪ ተንገብጋቢ ስለሆኑ ብቻ አሳቢ፣ ተፈሪ፣ ተቆርቋሪ፣ ጠባቂ ወገን ስለሌላቸው ያለ ወንጀላቸው ወንጀል ተፈጥሮላቸው ከገዛ ቀያቸው ዘሎ በገባ በመከላከያ ሠራዊትና በፌዴራል ታድነው በጥይት ተደብድበው በአሰቃቂ ሁኔታ በግፍ ይገደላሉ፡፡ በዚህች ሀገር አማራ ስትሆን እጣ ፋንታህ ይሄ ነው፡፡ አማራ ሆይ በእነኝህ በግፍ ሰለባ ልጆቹ በእነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌ የተፈጸመውን አረመኔያዊ ግፍ ያለ ተቃውሞ በዝምታ ተቀበልክ ማለት ከእስከአሁኑ በከፋ የግፍና የውርደት ኑሮ ለመኖር ተስማማህ ማለት እንደሆነ ዕወቅ!!!

እባካቹህ የወያኔ/ኢሕአዴግን ወሬ ፈጽሞ አትመኑ!!! የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዚህ ቀደም የነበሩትን አማራጭ የመረጃ ምንጮችን አሳጥቶ በራሱና የራሱ ባደረጋቸው በአሜሪካ ድምፅ፣ በጀርመን ድምፅ፣ በኢሳትና በሌሎችም የብዙኃን መገናኛዎች እየነዛው ያለው አንድ ዓይነት ወሬ ሁሉ ፈጽሞ ሐሰት ነው፡፡ ወያኔ/ኢሕአዴግ በከፍተኛ ዝግጅትና ቅንብር ይሄንን ድራማ የሠራበት ሁለት ዐበይት ምክንያቶች አሉ፡-

፩ኛው. የእነ ብ/ጄ አሳምነው ጽጌ አማራን የማነቃነቅ ቆፍጣና እንቅስቃሴ በእጅጉ ስላሠጋቸው በአጭር ለመቅጨት ታስቦ ነው ይሄ ደም ያፋሰሰ ድራማ የተቀናበረው!!! ከሥልጣኑ እንዳያነሡት ወይም እንዳይሽሩት ከአማራ ሕዝብ ጋር ሊጋጩ ወይም ሊጣሉ ሆነ ይሄንን ደግሞ አይፈልጉትም፡፡ አማራ "ለውጥ አለ!" ብሎ እንዳሰበ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ፡፡ ብ/ጄ አሳምነው ጽጌን ሻሩት ወይም አነሡት ማለት የሚያነሡበት ምክንያት በግልጽ ስለሚታወቅ እርምጃቸው የአማራ ሕዝብ ለውጡ ውሸት መሆኑን እንዲነቃ ስለሚያደርግ እንዲህ ማድረግ ስላልፈለጉ ነው በዚህ መልኩ ጀግናውን ብ/ጄ አሳምነው ጽጌንና ሌሎች ጀግኖች ጓዶቹን ማስወገድና የአማራን ንቅናቄ ማዳፈን የፈለጉበት ምክንያት፡፡

2ኛው ደግሞ በዚህ ሐሰተኛ ውንጀላ ከእነ ጄኔራል አሳምነው ጋር የተወነጀሉት ከእስር የተፈቱ የግፍ እስሰኞችና ከበረሃ ወይም ከትጥቅ ትግል የገቡ ወይም የተመለሱ አርበኞች ወይም ፋኖዎች እንደመሆናቸው እነዚህ ወገኖቻችን ለዲሞክራሲያዊ የሥርዓት ለውጥ ፈጽሞ ተገዥ ያልሆኑና ሥልጣንን በኃይል ብቻ መጨበጥ የሚፈልጉ አስመስሎ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በማሳየት በቀጣይ ጊዜ "ለውጥ!" የተባለው ውሸት መሆኑን እየተረዳ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ደግሞ የአማራ ሕዝብ በሚያደርገው የነጻነትና የህልውና ትግል ላይ ትግሉን ለማዳፈን ወያኔ በሕዝብ ላይ ለሚወስደው አረመኔያዊ ጥቃትና እርምጃዎች ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተቃውሞ እንዳይገጥመው አስቀድሞ አፍ ለማዘጋትና ወያኔ እነዚህን በሐሰት የወነጀላቸውን ወገኖቻችንን በፊትም ማሰሩ ትክክል እንደነበረና እስረኞቹን ከእስር መፍታቱ፣ በትጥቅ ትግል የነበሩትን ወደ ሀገር እንዲገቡ ማድረጉ ስሕተት እንደነበረ እንዲገነዘቡለት ለማድረግ በማሰብ ያደረገው እጅግ ሸፍጠኛ አጋንንታዊ ድራማ ነው፡፡

የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ውስጣችን ምን እንዳለ ማለትም ማን በዳይ ማን ተበዳይ፣ ማን ገፊ ማን ደግሞ ተገፊ፣ ማን ጥቃት አድራሽ ማን ደግሞ ተጠቂ፣ ማን ግፍ ተጋች ማን ደግሞ ግፍ አድራሽ እንደሆነ አያውቅምና ወያኔ እየቀመረ በሚረጨው ሐሰተኛ መረጃ የተሳሳተ ግንዛቤ መያዙ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ እናም የዚህ ደም አፋሳሽ የወያኔ ድራማ ዓላማው እነኝህ ሁለቱ ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ባለ አደራ ምክር ቤት (ባልደራስ) አባላትን "ባሕር ዳር ከተፈጸመው መፈንቅለ መንግሥት ጋር በተያያዘ ተጠርጥራቹሃል!" እያሉ ሰብስበው ማሰራቸው ራሱ የሚጠቁመው ነገር ባልደራስ "በባሕር ዳር ሕዝብ ጥያቄ!" በሚል የሸፋን ምክንያት ባሕር ዳር የተጋበዙት ሆን ተብሎ እነ ጄኔራል አሳምነውን "አደረጉት!" ከሚሉት የፈጠራ ወንጀል ጋር አያይዘው ወኅኒ ለማውረድ በማሰብ አስቀድመው ያዘጋጁትና ያቀዱት መሆኑን ያሳያል፡፡

እነ እስክንድር ባሕርዳር ሕዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ እንዳሰቡ ሲያስታውቁ በወቅቱ ይሄንን እንዲያስቡ ያደረጋቸው በዚያው ሰሞን እነ እስክንድርን ጠጋ ጠጋ ሲላቸው የነበረው የብአዴን ካድሬ መሆኑን ገልጬ ግብዣው የብአዴን ሸፍጥ ሊኖርበት እንደሚችል ገልጬ እነ እስክንድር ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስቤ ነበር፡፡ ያልኩት አልቀረም ይሄው እነ እስክንድር "በባሕርዳር ሕዝብ ጥያቄ!" በሚል ሐሰተኛ የሸፋን ምክንያት እነ እስክንድር ባሕርዳር የተጋበዙበት ዓላማ እነ እስክንድርን ከእነ ጄኔራል አሳምነው ጋር አገናኝቶ በመወንጀል ለማሰር በማሰብ እንደሆነ አሁን ግልጽ ሆኗል፡፡ እነ እስክንድር ባሕርዳር ሕዝባዊ ስብሰባ ሊያደርጉ እንደሆነ በፌስቡክ ላይ መጀመሪያ ላይ የገለጸውም ይሄው እራሱን የአማራ ብሔርተኛ አስመስሎ እየተንቀሳቀሰ ያለ ድብቅ የብአዴን ካድሬ ነው፡፡

ወደ እነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌ ስንመለስ እርግጥ ነው እነ አቶ አምባቸውን የገደሉ ወያኔ እንጅ እነ ብ/ጄ አሳምነው ጽጌ አይደሉም ስል ጉዳዩን በነጻነት ትግል ዓይን ካየነው እነ ጄኔራል አሳምነው እንዲህ ዓይነት ዘለዓለም የገዛ ወገናቸውን እያስበሉ የወያኔ ባንዳ ሆነው መቀጠል የሚፈልጉትን ክፉ ባንዳ የብአዴን ባለሥልጣናትን የማስወገድ በእነሱ ላይ እርምጃ የመውሰድ ፍላጎት ጨርሶ የላቸውም እያልኩ አይደለም፡፡ ጄኔራል አሳምነው በምዕራብ ጎንደር ወያኔና ቅጥረኞቹ የቅማንት ኮሚቴዎች ከመከላከያ ሠራዊት ጋር በመቀናጀት በአማራ ሕዝብ ላይ አረመኔያዊ ግፍ በፈጸሙ ጊዜ የያዛቸውንና በተለያየ መንገድ የገለጻቸውን ተጨባጭ መረጃዎችን ቅጥረኞቹ የብአዴን ባለሥልጣናት በክልሉ የብዙኃን መገናኛ እየወጡ ትንሽም ሳያፍሩ "ሐሰት ነው!" እያሉ ሲያስተባብሉበትና ወንጀለኞች ተጠያቂ እንዳይሆኑ ጥረት ሲያደርጉ ለወንጀላቸውም ተባባሪ

ሲሆኑ ካየ ጊዜ ጀምሮ በብአዴን ባለሥልጣናት ላይ ተስፋ ቆርጦና ፈጽሞ ለአማራ የማይቆሙ ቀንደኛ የአማራ ጠላቶች መሆናቸውን አውቆ በእጅጉ እየተብሰለሰለ እያረረ እየተቃጠለ ነው የቆየው፡፡

ከዚያ ጊዜም በኋላ በታዘባቸው ብዙ ነገሮች ብአዴን እሱን የክልሉ የጸጥታና ደኅንነት ኃላፊ አድርጎ የሾመው መጠቀሚያ ሊያደርገው እንጅ ብአዴን ስለተለወጠ እንዳልሾሙት፣ ለውጥ የተባለውም ሐሰት መሆኑን፣ አማራ ከመቸውም ጊዜ በላይ የህልውና አደጋና ውስብስብ ፈተና እንደተጋረጠበት በሒደት መረዳቱን በተለያዩ ጊዜያት ከተናገራቸው ንግግሮቹ መረዳት ይቻላል፡፡ አሁን ወደ መጨረሻማ ጭራሽ እነኝህ ለወያኔ ያደሩ የብአዴን ባለሥልጣናት "ፋኖ መመታት መደምሰስ አለበት!" እያሉ በይፋ በአደባባይ  ይናገሩ እንደነበረ የሚታወቅ ነው፡፡ ፋኖን ብቻ ሳይሆን በማኒፌስቶ አማራን የማጥፋት ዓላማ እንዳለው በግልጽ አውጀ የመጣውን ወያኔን ጨምሮ ሌሎችም አጎራባች ክልል ተብየዎች አማራን ማጥፋትንና ማጥቃትን ታሳቢ በማድረግ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ልዩ ኃይልና ሚኒሻ አሠልጥነው ዝግጁ ባደረጉበትና አሰማርተውም አማራን በየስፍራው እየፈጁ እያጠቁና በገፍ እያፈናቀሉ፣ እንደጦስ ዶሮ የትም እየደፉና እያረዱ ባሉበት ሁኔታ ከሰሞኑ ብአዴን አማራን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በሚሰነዘር ምት ለማስጠፋት ከጠላት ጋር በማሴር "ልዩ ኃይል አያስፈልገንም!" የሚል አቋም መያዙ ጀኔራል አሳምነውን በብአዴን ላይ የመጨረሻ ተስፋ እንዲቆርጥ አድርጎት ነበር፡፡

በዚህ በዚህ ምክንያት ነው ጀኔራል አሳምነው በወገኑ ላይ የሚሠራው ሸፍጥ፣ አሻጥር፣ ሴራ የሚፈጸመው ፍዳና ሰቆቃ፣ የሚዶለተው ዱለታ በእጅጉ አስከፍቶት ቀደም ሲል ጀምሮ በከፍተኛ እልህና ቁጭት በመነሣሣት የያዘውን አማራን ነጻ የማውጣት ጽኑ ፍላጎትና ታላቅ ዓላማ አጠናክሮ ከጓዶቹ ጋር መንቀሳቀስ ጀምሮ የነበረው፡፡ በመሆኑም እነ ጀኔራል አሳምነው ባንዳና የወያኔ አህያ ነቀርሳ የብአዴን ባለሥልጣናትን ማስወገድ መፈለጋቸው የሚያጠራጥር አይደለም!!!

ይሁንና ግን እነ ብ/ጄ አሳምነው ጽጌ ያለ በቂና አስተማማኝ ዝግጅት እንዲህ ዓይነት እርምጃ በመውሰድ ትግላቸው በአጭር እንዲቀጭና 2001 ዓ.ም. ላይ የሠሩትንና ከባድ ዋጋ ያስከፈላቸውን ስሕተት መልሰው ለመድገም ፍላጎት ይኖራቸዋል ብየ ፈጽሞ አልገምትም ወይም እንዲህ እንደማይሳሳቱ መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ!!! ነገሩን በአመክንዮ ዕይታ ስናየውም እነ ብ/ጄ አሳምነው ጽጌ እራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ሰጥተው ይሄንን ያህል ቆራጥ እርምጃ የመውሰድ ፍላጎት ካላቸው ፈጽሞ እንዲህ በቀላሉ የሚሰናከል ሙከራ እንደማያደርጉና ጊዜ ወስደው ደምበኛ ስትራቴጂ (ስልት) ነድፈው በሚገባ ተደራጅተው ሰልቀው በመሥራት ውጤታማ ሊያደርጋቸው የሚችል ሥራን ይሠራሉ እንጅ እንዲህ በቀላሉ የሚጨናገፍ ሥራ ሠርተው እንዋረድ ሊሉ አይችሉም!!! ሌላው ቢቀር እነ ንጉሡ ጥላሁን፣ እነ ደመቀ መኮንን፣ እነ ገዱ አንዳርጋቸው ባጠቃላይ ዘጠኙ የብአዴን ሥራ አስፈጻሚ አባላት እና አርባ አምስቱ የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የሚሰባሰቡበትን ቀን ጠብቆ ይፈጅልንና ከወያኔ ባንዶች ነጻ ያወጣን፣ የወያኔን ቀኝ እጆች ይቆርጥልን፣ የወያኔን የብረት ምርኩዞች አስጥልልን፣ የሚሊዮኖች ወገኖቻችንን ደም ይበቀልልን ነበር እንጅ ጭራሽ በእጁ ነበርን፣ አግቶን ነበር፣ ይዞን ነበር ምንንትስ ያሉ ባሕርዳር የነበሩ ከፍተኛ ፀረ አማራ የወያኔ ተቀጣሪ የብአዴን ባለሥልጣናትን እንኳ መግደል እየቻለ ሳይገላቸው ሊቀር አይችልም ነበር፡፡

ጀግኖቹ እነ ጀኔራል አሳምነው ጊዜ ካገኙ በደንብ ተደራጅተው አማራን ነጻ ሊያወጡ እንደሚችሉ ስለሚያውቅ ነው ከላይ እንዳልኳቹህ ወያኔ የእነ ጀኔራል አሳምነው ጽጌ አማራን የማነቃነቅ ቆፍጣና እንቅስቃሴ በእጅጉ ስላሠጋው ለመቅደምና በአጭር ለመቅጨት አስቦ እንዲህ ዓይነቱን ድራማ በማቀናበር ቀደም ሲል የአማራን ሕዝብ "ብአዴን ተለውጧል!" ብሎ አምኖ ብአዴንን እንዲቀበል ለማድረግ ወይም ለማታለል ሲል ሾሞት የነበረውን ጀኔራል አሳምነውንና ጓዶቹን ለማስወገድና

ዓላማቸውን ለማሰናከል ድራማውን አቀናጅቶ እርምጃውን የወሰደው፡፡ አስቀድመው ቅዳሜ ከጠዋት ጀምረው ባሕርዳርን በፌዴራል ፖሊስና በመከላከያ መጠርነፋቸው ብቻውን የሚገልጠው ሐቅ ቢኖር የተፈጸመው ነገር ሁሉ አስቀድሞ የታሰበበትና ግፉን የፈጸመውም አገዛዙ መሆኑን ነው!!! የፌዴራል ፖሊስና መከላከያ በምን ምክንያትና በማን ጥያቄ አስቀድመው እዚያ ሊገኙ ቻሉ???

እንደማየው ከሆነ ግን ወያኔ/ኢሕአዴግ በብዙኃን መገናኛዎቹ ድራማውን እውነት አስመስሎ ደጋግሞ በመለፈፉ ሕዝቡ ድራማውን እውነት አድርጎ የተቀበለ ይመስላል፡፡

መጀመሪያ ላይ ጀኔራል አሳምነው ጽጌ "ተሠውሯል!" ወይም "አምልጧል!" መባሉም አብዛኛውን ሰው "ከተሠወረስ አድርጎታል ማለት ነው!" እንዲል አድርጎት ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ለዚህ እንዲመቻቸው መሰንበቻውን ከእነ ጀኔራል አሳምነው ጋር በተያያዘ ሲያስወሩት የነበሩት ነገሮች ስለነበሩ ሰው ይሄንን ጉዳይ ከዚያ ጋር እያገናኘ ድራማውን እውነት አድርጎ ሊቀበል ችሏል፡፡ ቆይ ግን እና ታዲያ በሐሰት ወንጅለው መቀመቅ ሊያወርዱት እንደሆነ እያወቀ እጅ መስጠት ነበረበት ወይ???

ከብቶቹ የተቀሩት የብአዴን ባለሥልጣናት ከዚህ በእነ አምባቸው ላይ ወያኔ ከወሰደው የግፍ እርምጃ መውሰድ የሚገባቸው ትምህርት ቢኖር ወያኔን "አሜን ወዴት!" ብለው ቢያገለግሉትም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማንኛውም ጊዜ በየትኛውም ቦታ ድራማ አቀናብሮ በእነ አቶ አምባቸው ላይ እንደወሰደው ዓይነት እርምጃ በመውሰድ እያንዳንድሽንም የሚደፋሽ መሆንሽን አውቀሽ ሞት ካልቀረልሽ ለወገንሽ ታግለሽ የክብር ሞት መሞት አማራጭ የሌለው በሳልና ትክክለኛ ውሳኔ መሆኑን ነው!!!

የወያኔን ታሪክ እንደምታውቁት በእንዲህ ዓይነት የመበላላት አሻጥር ወይም ሴራ የተሞላ ነው፡፡ ወያኔ እንኳንና ለባዕዶቹ ለእነ አምባቸው መኮንን ይቅርና ለገዛ ወገኖቹና ታጋዮቹ እንኳ ሳያዝን ድርጅቱን ተጠቃሚ የሚያደርገው መስሎ ከታየው ስንቱን መሥዋዕት እያደረገ እየበላ የመጣ አውሬ ነው፡፡

በእነ ሠዓረ ሞት ዙሪያ ከታች ያስቀመጥኩትን ከወደ ባሕርዳር የወጣ መረጃ ከመስማቴ በፊት የእነ ሠዓረ አሟሟት ጉዳይ የእኔ መላምቶች የነበሩት መጀመሪያ ደረጃ "ተገደሉ!" ብሎ ወያኔ የረጨውን ዜና አላመንኩትም፡፡ ማለቴ ወያኔ ምሥጢሩን በጣት በሚቆጠሩ ሰዎቹ እንዲያዝ በማድረግ ሠዓረንና ገዛኢን መቀሌ ወስዶ ከደበቀ በኋላ ከላይ ለገለጽኩላቹህ ዓላማ "ተገደሉ!" ብሎ በሐሰት ያስወራ ይመስለኛል፡፡ ድንጋይ የተሞላበት አስከሬን የሌለው የሬሳ ሳጥን አሽክሞ ነው ሲተውንብንና ቤተሰብ ዘመዶቻቸውን በዕንባ ሲያራጭ የነበረው፡፡ አስከሬናቸውን በዐይኑ በብረቱ ካየ እውነተኛ የመረጃ ምንጭ ካላረጋገጥን በስተቀር "ሞቱ!" ወይም "ተገደሉ!" መባሉን ማመን አይኖርብንም!!!

መሞታቸው እውነት ከሆነ ደግሞ ከላይ በሁለተኛ ደረጃ ከገለጽኩላቹህ በተጨማሪ ወያኔ እነ ጀኔራል አሳምነውን እነ አንባቸውን ገደሉ ብሎ የወነጀለበትን ድራማ ፍጹም እውነት ለማስመሰል ማለትም ሕዝቡ "ትግሬ ከተገደለስ እውነት ነው ማለት ነው!" እንዲል ለማድረግ፣ አማራ ብቻ መገደሉ የአማራን ሕዝብ ሊያስነሣ ይችላል ተብሎ በመገመቱ ስሜት ለማብረጃነትና ሚዛን ለመጠበቅ፣ ትግሬ ግልጽና አሁናዊ አደጋ (clear and present danger) የተጋረጠበት ለማስመሰል በእነዚህ ምክንያቶች እንዲሞቱ የፈረደባቸውና እራሱም የገደላቸው ናቸው የሚል ግምት ነበረኝ፡፡

ምክንያቱም ትግሬ የሠዓረ የግል ጠባቂ የአማራን ትግል ለማገዝ ወይም የእነ ጀኔራል አሳምነውን ግብረአበር ሆኖ እነ ሠዓረን ይገላል ብሎ ማሰብ ሲበዛ ቂልነትና ፈጽሞ የማይመስል ነውና፡፡ እነ ጀኔራል አሳምነውም ትግሬ የሠዓረን የግል ጠባቂ

"የመንግሥት ግልበጣ ልናደርግ ነውና አንተም ተባብረኸን እነ ሠዓረን ግደልልን?" ብለው የሚያማክሩ ወይም የሚጠይቁና ምሥጢራቸው ጉዳዩን ከመፈጸማቸው በፊት ወጥቶ ተለቃቅመው እንዲታሰሩ ዕድል የሚሰጡ ቂሎች አይደሉምና፡፡ ከላይ ለጠቀስኩት ፖለቲካዊ ጥቅማቸው እራሳቸው ከነ የግል ጠባቂው ገለው ሲያበቁ ነው "የግል ጠባቂያቸው እነ ሠዓረን ገሎ እራሱን አጠፋ!" የሚሉን የሚል ግምት ነው የነበረኝ፡፡ collateral damage ይለዋል ፈረንጅ እንዲህ ዓይነቱን አማራጭ ስለሌለ በሚወሰድ እርምጃ በራስ ወገን ላይ የሚደርስ ያልተፈለገ ጉዳትን፡፡

የኔ ግምት ይሄ ነበር፡፡ ከወደ ባሕርዳር የተሰማው ግን ሠዓረ መኮንን፣ ገዛኢ አበራና የሠዓረ የግል ጠባቂ እንዲሁም ሌሎች ስማቸው ያልተገለጸ ከእነ ሠዓረ ጋር አብረው እነ አምባቸውን ለመግደል የሔዱ ወታደሮች የተገደሉት ባሕርዳር ሲሆን አገዳደላቸውም የድራማቸውን ተልእኮ ማለትም እነ አምባቸውን እራሳቸው ገለው ሲያበቁ እዛው ሳሉ እነ ጄኔራል አሳምነውን የገደሉ አስመስለው በመወንጀል በእነ ጄኔራል አሳምነው ላይ እርምጃ ሊወስዱባቸው ሲንቀሳቀሱ እነ ጄኔራል አሳምነው በወሰዱት እራስን የመከላከል እርምጃ የተገደሉ ወይም ቅምጥ ቅምጣቸውን ተብለው የተደፉ መሆናቸው ነው የተሰማው፡፡

ወያኔዎች የእነ ሠዓረ አሟሟት ለወሬ አልመች ስላላቸው፣ ሽንፈታቸውን የሚያሳይ ውርደት፣ ቅስማቸውን የሚሰብር ጥቃት ሲሆንባቸውና ነገሩ ድራማቸውንም የሚያጋልጥ ሲሆንባቸው ጊዜ ነው እሬሳቸውን አዲስ አበባ አምጥተው ሲያበቁ "በግል ጠባቂያቸው ተገደሉ!" የሚል ወሬ የነዙት፡፡ "እነ ሠዓረ የትግሬ ተወላጅ በሆነው የግል ጠባቂያቸው የእነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌ የመንግሥት ግልበጣ ግብረአበር ሆኖ ተገደሉ!" የሚለው ወሬ ፈጽሞ የማይመስል ከመሆኑ የተነሣ ይሄ ከወደ ባሕርዳር የተሰማው ዜና ትክክለኛ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ወያኔ በኋላ ላይ ደግሞ እንደገና የሚሰጠው ሐሰተኛ መረጃ ሲሳከርበት ጊዜ እነ ሠዓረን "ገደለ!" ያሉትን የሠዓረን የግል ጠባቂ "እራሱን አጠፋ የተባለው በስሕተት ነው ቆስሎ ሆስፒታል ነው ያለው!" ብለዋል፡፡ እንግዲህ ባሕርዳር ከቆሰሉት ቁስለኞቻቸው አንዱን ምናልባትም አማራ የሆነውን አቅርበው ሊያስዋሹ አስበዋል ማለት ነው፡፡ የዚህ ድራማ ተባባሪዎች ስለሆኑና ለራሳቸውም ስለሚፈሩ ፈጽሞ ትንፍሽ አይሏትም እንጅ ድራማውን በዓይናቸው ያዩ የብአዴን ባለሥልጣናት እውነቱን ያውቁታል፡፡

"ስብሰባው ውስጥ ነበርን" ያሉ ከሰባቱ ሦስቱ የብአዴን ባለሥልጣናት በቴሌቪዥን ቀርበው ስለሁኔታውና እነሱ እንዴት ሊተርፉ እንደቻሉ ሲናገሩ እንደሰማቹሃቸው በርካታ ጥርጣሬ የሚያጭሩ ነገሮችን ተናግረዋል፡፡ ስብሰባ ላይ እንዳሉ ሦስት የታጠቁ የልዩ ኃይል አባላት መጥተው ከውጭ የተለየ ድምፅ ስላሰሙ ከመሀላቸው አንዱ እዘዝ ዋሴ የተባለው በሩን ከፍተው እንዳይገቡ ጠርቅሞ እንደያዘው፣ በመስኮት በኩል ማምለጥ ቢፈልጉም ሌሎች የልዩ ኃይል አባላት በመስኮት በኩልም ስለነበሩ በመስኮት ማምለጡን እንደተውት ተናገሩ፡፡

ከዚያ አምባቸው፣ ምግባሩና በሩን ጠርቅሞ ያዘ የተባለው እዘዝ በየት በኩል ከእነሱ ተነጥለው ወጥተው እንደሔዱ ሽፋፍነው በኋላ ላይ ሌላ ክፍል ውስጥ አምባቸውና እዘዝ ሞተው ምግባሩ ቆስሎ ሲያጣጥር እንዳገኟቸው ተናገሩ፡፡ እነሱ ግን እዚያው ሟች እዘዝ ዋሴ "በሩን ጠርቅሞ ያዘው!" ካሉት ክፍል በመቆየታቸው እንደተረፉ ተናገሩ፡፡ ለእኛ የተነገረን ሰባቱም በአንድ ክፍል ውስጥ ስብሰባ በነበሩበት ግድያው መፈጸሙን ነው፡፡ እነዚህ የሚሉት ደግሞ መጀመሪያ "አብረን ነበርን!" ካሉ በኋላ "እናንተ እንዴት ልትተርፉ ቻላቹህ?" ቢባሉ የሚመልሱት ስለሌለ ሟቾቹ ሌላ ክፍል እንደሞቱ ይናገራሉ፡፡ በሩን ጠርቅሞ የያዘው እዘዝ ዋሴ ከሆነ እንዴት ሌላ ክፍል ላይ ሔዶ ሊገደል ቻለ??? የሚገርመው ነገር ደግሞ ሊገሉ የመጡ ወታደሮች ያውም በአንድ ሰው ብቻ በሩ ተጠርቅሞ ስለተያዘባቸው መግባት ሳይችሉ መቅረታቸው ነው፡፡

አሁን ይሄ ምኑ እውነት ይመስላል??? በር ከፍተው ካላዩዋቸውስ ሦስት መሆናቸውን እንዴት አወቁ??? ለወታደር አይደለም ለአንድ ተራ ሰው በአንድ ሰው ተጠርቅሞ የተያዘን በር በእርግጫ በርግዶ መግባት ያቅተዋል ወይ??? እሽ እርግጫውም ይቅር ሊገሉ የመጡ ወታደሮች ናቸውና በያዙት መሣሪያ በሩን በጠብመንጃቸው ተኩሰው በመበታተን መግባት ያቅታቸዋል ወይ???

ሌላው ደግሞ የክልሉ ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አሰማኸኝ ወደ የእንግዶች ማረፊያ (Guest house) ሲሔድ መንገዱ ላይ አልፎት የሚሔደው የርእሰ መሥተዳድሩ ግቢ ሰላማዊና በአካባቢው ምንም ዓይነት ችግር ያልነበረ መሆኑን ገልጾ ከእንግዶች ማረፊያ ሲደርስም ጄኔራል አሳምነው ጽጌን ከልዩ ኃይሉ ጋር ከዚያ እንዳገኛቸውና እስከ ምሽቱ አራት ሰዓትም እዚያ እንደነበሩ የዓይን ምስክር ነኝ ብሎ ሲናገር እነዚህ ከሟቾቹ ከእነ አምባቸው ጋር ስብሰባ ተቀምጠን ነበር የሚሉት ደግሞ "11 ሰዓት ላይ ስብሰባ ተቀምጠን በነበርንበት ሰዓት ጄኔራል አሳምነው ልዩ ኃይሉን ይዞ መጥቶ ነው ጥቃቱን የፈጸሙብን!" ብለው ተናግረዋል፡፡

የትኛው ነው ትክክል??? አቶ አሰማኸኝ እንዳለው አልፎ ሲሔድ እንዳየው የርእሰ መሥተዳድሩ ግቢ ሰላም የነበረ ከሆነና እሱ ከእንግዶች ማረፊያ ግቢ ከተገኘበት ሰዓት ጀምሮም እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ድረስ ጄኔራል አሳምነው እዚያ የነበረ ከሆነ "ከሟቾቹ ከእነ አምባቸው መኮንን ጋር 11 ሰዓት ላይ ስብሰባ ተቀምጠን ነበርን!" የሚሉት ሰዎች "ስብሰባ ተቀምጠን በነበረበት ሰዓት ነው ጄኔራል አሳምነው ልዩ ኃይሉን ይዞ መጥቶ ጥቃቱን የፈጸሙብን!" ያሉት ነገር ሙሉ በሙሉ ውሸት ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የርእሰ መሥተዳድሩ ግቢ ችግር ተፈጠረ የተባለው ፖሊስ ኮሚሽን ላይ ተፈጠረ ከተባለው ችግር በኋላ ነውና፡፡ ባጠቃላይ ምንም የማይመስል ነገር ነው "በሉ!" የተባሉትን ነው የተናገሩት፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ እስኪያቅርህ ድረስ ገና ብዙ የምታያቸው ተመሳሳይ ደም አፋሳሽ ድራማዎች አሉህ ጠብቅ፡፡ ገና እነ ዐቢይንም ይገሏቸዋል፡፡ ወያኔ ወደሥልጣን የመመለሻ (በርግጥ ወያኔ አሁን ከሥልጣን ተባሯል ማለቴ አይደለም እሱው ነው እነ ዐቢይን እያዘዘ የሚያሠራቸው፡፡ ነገር ግን እንደበፊቱ በግልጽ ማለቴ ነው) እናም ወደሥልጣን መመለሻው ብቸኛው መንገዱ በዐቢይ ላይ ግድያ ፈጽሞ ሲያበቃ "ግድያ ተፈጸመበት!" ብሎ "የአመራር ክፍተቱን ለመሙላትና ሀገር ለማረጋጋት!" በሚል ሰበብ መመለስ ስለሆነ ይሄ "ለውጥ!" የሚባለው የድራማ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በገዛ ቅጥረኛው ዐቢይ ላይ ተመሳሳይ ድራማ ሠርተው በማስገደል እንደገና እነሱው እራሳቸው ሁኔታውን አረጋጊ ሆነው በመቅረብ ነው ተዋንያኖቻቸውን እነ ዐቢይን አስወግደው እነሱው መልሰው የሚቀመጡት፡፡ ይህችን ጠብቁ!!!

እኔን የደም እንባ ያስለቀሰኝ፣ ያንገበገበኝና ያሳረረኝ የጀግናው፣ የአንበሳው፣ የአንጀት አርሱ፣ የአማራ የቁርጥ ቀን ልጁ የጀኔራል አሳምነው ጽጌና የሌሎች ጀግኖች ቆራጦች ጓዶቹ መሠዋት ነው እንጅ እነ አምባቸው በመገደላቸውም ሆነ እነ ዐቢይም በተመሳሳይ ድራማ የሚገደሉ በመሆናቸው ግን አላዝንም ይልቁንም ደስተኛ ነኝ፡፡ ለእንዲህ ዓይነት አሳዛኝ መጨረሻ ለሆዳቸው ሲሉ ለወያኔ አድረው የገዛ ወገናቸውን እያረዱና እያሳረዱ፣ እየበሉና እያስበሉ አውሬውን ወያኔን ሲያገለግሉ የኖሩና እያገለገሉም ያሉ በመሆናቸው ለእንደእነዚህ ዓይነቶች ባንዳ ከጠላትም ጠላቶች ቅንጣት ታክል ሐዘኔታም ሆነ ርሕራሔ የለኝም!!! ነፍሳቸውንም ይማረው ብየም አልመኝም!!!

የስንት ንጹሐን ወገኖቻችንን ነፍስ የበሉና ያስበሉ ሆነው እያለ እኔ "ነፍሳቸውን ይማረው!" ብልስ ፈጣሪ ይምራቸዋል እንዴ??? ስለዚህም ለምን እዋሻለሁ??? ለምን እራሴንም ሰውንም እሸነግላለሁ??? ጠላታችን የሆኑት በሚያገለግሉት ጠላታችን ስለተደፉልን እደሰታለሁ እንጅ!!! ቤተሰቦቻቸውን ግን ከሐዘናቸው እግዚአብሔር ያጽናቸው!!! ነፍሳቸውን ይማር የምለው ለአሳረኛው አማራ ወገናቸው የተሠውብንን ውድ ክቡር ብርቅና ድንቅ የሆኑትን እነ ጀኔራል አሳምነው ጽጌን ነው!!!

ርሕራሔ ወይም ሐዘኔታ ስለሌለኝ እንዳይመስላቹህ በእነ አምባቸው ሞት የተደሰትኩት ወይም ያላዘንኩላቸው፡፡ ነፍስ ካለው እንስሳ ሞት ባለፈም ዛፍ ሲቆረጥ የሚያስለቅሰኝ የዋህ ሰው ነኝ፡፡ እንዲህ ዓይነት ለግዑዝ እንኳ የማለቅስ ሰው ሆኘ እያለሁ ግን የሰው ፍጡር ለሆኑት ለብአዴን ሰዎች ቅንጣት ታክል ሐዘኔታ የለኝም፡፡ ምክንያቱም አማራ የሆኑ የብአዴን ሰዎች እራሳቸው አማራ ሆነው እያለ ፀረ አማራ የወያኔን መርዘኛ የጥላቻ ስብከት ጠጥተው የገዛ ወገናቸውን ለወያኔ/ትግሬ ጥቅም ሲሉ ሲፈጁና ሲያስፈጁ፣ ሲያርዱና ሲያሳርዱ የኖሩና አሁንም ያሉ በመሆናቸው፣ ሊያስመስሉ ይችሉ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ ፀረ አማራ ኢጋንንታዊ ልክፍታቸውም መቸም ቢሆን ፈጽሞ ሊድኑ ሊፈወሱ ደማይችሉ እርኩሶች፣ ቆሻሾች፣ ጭንጋፎች፣ ባንዶች መሆናቸውን ጠንቅቄ ስለማውቅ ነው!!!

በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስተላለፍ የምፈልገው ጥብቅ መልእክት፦የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ድራማው የተፈጸመበትና በዚህ እርምጃ ለሙብቱና ለህልውናው እያደረገው ያለውን ትግል ለመምታትና ለማጨናገፍ የታሰበበት የአማራ ሕዝብ ጉዳዩ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ አጥብቆ መጠየቅ አለበት፡፡ ይሄንን ጉዳይ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ማድረግ ካልተቻለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘለዓለም የወያኔ ደም አፋሳሽ ድራማዎች መጫወቻ ሆነህ መቅረትህ እንደሆነ እወቀው!!! በተለይ ደግሞ ኢላማው የአማራ ሕዝብ ደግሞ የጀመርከው የትግል መነቃቃትና ለሙብትህ ለህልውናህ መቆምህ መቀበሩ፣ እስክትጠፋ ድረስ የወያኔና ሌሎች የጥፋት ኃይሎች ግፍ መጫወቻና መቀለጃ መሆንህ መቀጠሉ እንደሆነ እወቀው!!! ወያኔ "የጀኔራል አሳምነው ግብረአበሮች ናቸው!" እያለ ፋኖዎችህንና እንደ እነ ሙቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ ያሉትን ባጠቃላይ በአማራ የህልውና ትግል ላይ ንቁ ተሳትፎ እያደረገ ያለውን በሙሉ በሐሰት እየወነጀለ ለቃቅሞ ያስራልና!!!

የአማራ ሕዝብ የነበረን ዕድል ፈጥነን የነበረንን ጊዜ ተጠቅመን ከእነ ጀኔራል አሳምነውና ፋኖዎች ጎን በመሰለፍ ተፋልሞ ነጻ መውጣት ነበር፡፡ አብን የሚባል አጃጃይ ቅጥረኛ የብአዴን ካድሬዎች ስብስብ "ከአዴፓ ጋር ወደፊት!" እያለ ሕዝቡን በማዘናጋቱና በማጃጃሉ አማራ ተዘናግቶ ወርቃማ ዕድሉን ሳይጠቀምበት እንዲቀር ተደረገ፡፡ ከዚህ በኋላማ እንደለመደብህ ፍዳህን መብላት ነው እንጅ ምን መፈናፈኛ ይኖርህ ይመስልሀል ወገኔ??? በመታለልና በመዘናጋት ተረጋግተህ መቀመጥህና ጊዜ መስጠትህ የሚጠቅመው ጠላቶችህን እንጅ አንተን አለመሆኑን መረዳት አልቻልክም፡፡ ከነአካቴውም ጠላቶችህ ምን ዓይነት ጠላት እንደሆኑ ልታውቃቸው አልቻልክም፡፡ ይሄ ዛሬም ወደፊትም ከባድ ዋጋ ያስከፍልሃል!!!

እርግጥ ነው ወያኔ/ኢሕአዴግ ጉዱ እንዲወጣ ፈጽሞ አይፈልግምና በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ይፈቅዳል ማለቴ አይደለም፡፡ እንደምታስታውሱት ለውጥ የተባለው ድራማ ከተጀመረ ወዲህ እንኳ ከቡራዩ አዲስ አበባ ጋር በተያያዘ በተሠራው ተመሳሳይ ደም አፋሳሽ ድራማ በደረሰው አደጋ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ጥሪ ቢያቀርብም በወያኔ የሚታዘዘው የዐቢይ አሥተዳደር አሻፈረኝ ብሎ መቅረቱ ይታወሳል፡፡

በወቅቱ ይሄንን የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጥያቄን የፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ እንዲሰጡትና እነሱም ጥያቄውን ጥያቄያቸው አድርገው እንዲያቀርቡ ጥሪ አቅርቤ ነበረ፡፡ እንደምታውቁት አንድ እንኳ የሚረባ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ባለመኖሩ

ጥያቄው ሳይቀርብ ቀረና ጉዳዩ በገለልተኛ አካል ሳይጣራ በመቅረቱ፣ የአገዛዙ ግፈኛ አሻጥር ባለመጋለጡ ይሄው ዛሬም ለእንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ አደጋ ልንዳረግ ችለናል፡፡

በመሆኑም በመላ ዓለም ያላቹህ ኢትዮጵያውያን በቀጣይ ጊዜያት ሕዝባቹህ እንዲህ በወያኔ አሻጥረኛ የንጹሐን ደም የሚጎርፍባቸው ድራማዎች ለከፉ ጉዳቶችና ኪሳራዎች ከመዳረጉ በፊት በኃያላን መንግሥታት ላይ ጫና ፈጥራቹህ ድርጊቶቹ በገለልተኛ አካል እንዲጣሩ ወያኔን እንዲያስገድዱ ብታደርጉልን በቀጣይ ጊዜያት ወያኔ/ኢሕአዴግ ሊያደርጋቸው ካሰባቸው ተመሳሳይ አሻጥረኛ ደም አፋሳሽ ድራማዎች ከሚያስከትሉት አደጋዎች ታደጋቹህን ማለት ነውና በተለይ በውጭ ሀገራት ያላቹህ ኢትዮጵያውያን እባካቹህ በርቱና ይሄንን አድርጉልን???

እዚህ ሀገር ውስጥ ግን ወያኔ ይሄንን ያደረገበት ምክንያት አንድም በዚህ አሳብቦ ለውጥ በሚለው ድራማው የሰጠውን የውሸት ነጻነት ትቶ ወደቀደመው አንባገነናዊ ፈላጭቆራጭ አገዛዝ ለመመለስ በመሆኑ ሕዝቡ በነጻ ማሰብ፣ በነጻ መናገር፣ ወይም በነጻ ሐሳብን መግለጽ፣ በነጻ መንቀሳቀስና መደራጀት የማይችል በመሆኑ፣ ሕዝቡ የለውጡን ውሸትነት ተረድቶ እንደገና ተቃውሞን እስኪያቀጣጥል ድረስ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ፈጥኖ ሊንቀሳቀስ አይችልምና፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞቻችንም እንደ የፖለቲካ ሰውና የፖለቲካ ድርጅት "ጉዳዩ በገለልተኛ አካል ከተጣራ በኋላ ያለንን አቋም እናሳውቃለን!" ማለት ሲጠበቅባቸው ያልበሰሉና ዘገምተኞች በመሆናቸው እንደሰማቹሃቸው ለአንዲት ቀን እንኳ እውነት ተናግሮ የማያውቀውን የአገዛዙን ሐሰተኛ ወሬ እንዳለ ሳያለምጡ ውጠው በየመግለጫቸውና በየቃለመጠይቃቸው በነጻነት ታጋዮቹና በግፍ ሰለባዎቹ በእነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌ ላይ የውግዘት መዓት የሚያዘንቡ ሆነዋልና ይሄንን ይሄንን ጉዳይ ግምት ውስጥ በማስገባት እባካቹህ ፈጥናቹህ ተንቀሳቀሱ???

በመጨረሻም "ልዩነትንና ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ በመነጋገር፣ በሐሳብ ልዕልና አምኖ በሐሳብ ክርክር መፍታት እየተቻለ በ 21 ኛው መቶ ክ/ዘ ፍላጎትን በኃይል በጉልበት በመግደል ለማስፈጸም መሞከር ኋላቀርነት፣ አለመሠልጠን ነው፣ አረመኔነት ነው....!" እያሉ ይወሸክቱ የነበሩ "የሃይማኖት መሪዎች ነን፣ ምሁራን ነን፣ የሀገር ሽማግሌ ነን፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ወይም ፖለቲከኞች ነን!" በሚል እየቀረቡ ይወሸክቱ ለነበሩ ደናቁርት የወያኔ ቅጥረኞች አንድ ጥያቄ ልጠይቅ፦

ሲጀመር የተባለው እውነት ለመሆኑ በምን አረጋገጣቹህ??? በቦታው ነበራቹህ??? ሲቀጥል ደግሞ በትክክል የተፈጸመ ቢሆን እንኳ እነ ጄኔራል አሳምነው ይሄንን ችግር ለወያኔ ካደሩ ቅጥረኛ የብአዴን ባለሥልጣናት ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ በመነጋገርና የሐሳብ ክርክር በማድረግ መፍታት የሚችሉ ቢሆን ኖሮ የቤተሰብ ኃላፊዎች ሆነው እያለ አደገኛ ከሆነና ውድ የሕይወት ዋጋ ከሚያስከፍል ጣጣ ውስጥ መግባት የሚፈልጉ ይመስላቹሃል ወይ??? ከመቸ ወዲህ ነው በወያኔ/ኢሕአዴግ ቤት በሐሳብ ልዕልና ታምኖ በሐሳብ ለመሸነፍ የሚፈቅድ ነጻ መድረክና ሥርዓት ሥራ ላይ የዋለው??? የወያኔ/ኢሕአዴግ ተፈጥሮ ይሄንን ይፈቅዳል ወይ??? ምን ዘገምተኛና ደናቁርት ብትሆኑ ነው በሌለ ነገር ላይ እንዲህ ልትፈርዱ የቻላቹህት???

በተጨማሪም የኢሳት ጋዜጠኞችን ጨምሮ በየሚዲያው በምሁራን ስም የሚቀርቡ ደናቁርት የወያኔ ቅጥረኞች ሶሻል ሚዲያ ተዘግቶ መቆየት እንዳለበት ሲመክሩ ይሰማሉ፡፡ ለእነኝህ ደናቁርት ማለት የምፈልገው ነገር ቢኖር ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሀገር ሰላምና ደኅንነት ዋስትናው እንደዚህ ዓይነት ወያኔ/ኢሕአዴግ የሚፈጽማቸው ሕዝብን የሚያስቆጡ የግፍ ግድያዎች፣ የፖለቲካ ሴራዎች፣ ማፈናቀሎች ወዘተረፈ. ሙሉ ለሙሉ እንዲቆሙ መደረጋቸው ነው እንጅ አፈና አይደለም፡፡ መቸም ጊዜ የትም ቦታ ቢሆን ፈጽሞ አፈና መፍትሔ ሆኖ አያውቅም፡፡ በተለይ "ምሁር ነኝ!" የሚሉ ግለሰቦች አፈናን መፍትሔ አድርገው ሲመክሩ ዝቅጠት ውስጥ መሆናቸውን አመላካች እንደሆነ ይወቁት፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ ግፍ የተሞላባቸው

የፖለቲካ አሻጥሮች፣ ግድያዎች፣ ማፈናቀሎች፣ የመብት እረገጣዎችና ገፈፋዎች ወዘተረፈ. እስካሉ ጊዜ ድረስ ሶሻል ሚዲያው ብቻ አይደለም አጠቃላይ ሚዲያ የተባለ ሁሉ ተጠርቅሞ ቢዘጋም እንኳ ከቶውንም ቢሆን ሰላምና ደኅንነት ሊኖር አይችልም!!! በጥንት ዘመን ህገራት ሰላምና ደኅንነት ያጡ የነበሩት ሶሻል ሚዲያ ስለነበረ አይደለም ግፍና በደል ስላለ እንጅ!!!

ስለሆነም ማሰብና ማስተዋል የተሳናቸው እነኝህ ቅጥረኛ ግለሰቦች ወያኔ/ኢሕአዴግን እየመከሩ ያሉት "የቻልከውን ያህል የምትፈጽመውን ግፍ ለሕዝብ እንዳይገለጥ፣ ለአደባባይ እንዳይበቃ እያደረክ አፍነህ ፈጽም አድርግ!" ብለው እየመከሩት እንደሆነ ይወቁት፡፡ "ምን ያለበት ዝላይ አይችልም!" ካልሆነ በስተቀር ወያኔ/ኢሕአዴግ በሕዝብ ላይ የሚፈጽመው ግፍ፣ አሻጥር፣ ጥቃት፣ ረገጣ፣ የመብት ገፈፋ፣ ዝርፊያ ወዘተረፈ. እስከሌለ ጊዜ ድረስ ሶሻል ሚዲያው ሊያወራው ሊያራግበው የሚችለውና ለሀገር ሰላምና ደኅንነት ሥጋት ሊፈጥር የሚችል አንድም ነገር ሊኖር አይችልምና፡፡ ዕኩይ ዓላማ ያዘሉ ሐሰተኛ መረጃዎች ይራገባሉና ተብሎ ለእውነተኛ መረጃዎችም መድረክ ማሳጣት ዕድል መንፈግ ሽፍጥ ነው፡፡ በሶሻል ሚዲያ የሚለቀቁትን ዕኩይ ዓላማ ያዘሉ ሐሰተኛ መረጃዎች ዋጋ እንዲያጡና ሰሚ እንዳይኖራቸው ማድረግ የሚቻለው እውነቱን በማውጣት፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በማስፈን፣ የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ እንጅ እውነተኛ መረጃዎችም ሊስተናገዱበት የሚችለውን መድረክ እንዲጠፋ በማድረግ አይደለም! እሳት ያቃጥላል አጥፊ ነው ተብሎ እሳት ይጥፋና ማብሰያ እንጣ እንላለን ወይ??? እውነት እንዲያሸንፍ ከተፈለገ ምንም ዓይነት አፈና መኖር የለበትም! እውነት ካላሸነፈ ደግሞ መቸም ቢሆን ሰላምና መረጋጋት ሊኖር አይችልም! አፈናን የሚመርጥ ከእውነት ጋር የተጣላና እውነትን የሚፈራ ብቻ ነው!!! ገባቹህ ይሆን እነ ደናቁርት???

ከሁሉ በጣም የገረመኝ ደግሞ ምንም የማያውቀውን የአማራ ገበሬ አማራ ስለሆኑ ብቻ በፈለገ ጊዜ ሁሉ የትም ያለ ርሕራሔ ሲጨፈጭፍ የኖረውና አሁንም የሚጨፈጭፈው የዜጎችን ነፍስ ከምንም የማይቆጥረው መከላከያ ሠራዊት ተብየው የወያኔ ጭፍራ የጦር መሪዎች በሐሰት የተወነጀሉትን እነ ጄኔራል አሳምነውን "በመግደል የሚያምኑ አረመኔዎች!" እያሉ ለመኮነን ለማውገዝ አፋቸውን ሲከፍቱ ማየቴ ነው፡፡ ለማያውቅሽ ታጠኝ አለ ያገሬ ሰው!!!

በተረፈ አጋጣሚው ብርቅ፣ ድንቅ፣ አኩሪ ጄኔራል አሳምነውንና ቆራጥ ጓዶቹን ጀግኖቻችንን አርበኞቻችንን ያጣንበት ቢሆንም ጀግኖቻችን ከላይ እንደተገለጸው እራስን በመከላከል እርምጃቸው ሊገላቸው የሔደውን ነቀርሳ የወያኔ ጭፍራ ከነ አውራው በመንቀል ከፈጸሙልን ጀብድና ውለታ በተጨማሪ፡-

* በአማራ ሕዝብ ስም ይነግዱ የነበሩ አብን፣ መአሕፓ፣ መኢአድ ሌሎችም አስመሳይ ድርጅቶች እና ትልልቅ ስም ያላቸው ያልታወቀባቸውና እራሳቸውን የሸጡ ቅጥረኛ ግለሰቦች ሁሉ እንደሰማቹሃቸው መጀመሪያ አካባቢ እነ ጄኔራል አሳምነውን እየኮነኑና እያወገዙ "አስፈላጊ በሆነው ሁሉ መንግሥትን እንተባበራለን ከመንግሥት ጎን ነን!" እያሉ ጭራሽ የአማራ ሕዝብም "መንግሥት!" ከሚሉት ፀረ አማራ አገዛዝ ጋር እንዲተባበር ጥሪ በማቅረብ ከፀረ አማራው አገዛዝ ጎን መሆናቸውን ሲገልጡ ቆዩ ኋላ ላይ ደግሞ የአማራ ሕዝብ የተፈጸመበትን ግፍ የተሞላ አሻጥር በራሱ መንገድ እንዳወቀ ሲረዱ ጥቃቱን ማን እንደፈጸመው ሳይገልጡ የአማራን አንድነት ለመከፋፈል የተፈጸመ ጥቃት እንደሆነ መንዛት ቀጠሉ፡፡ ሲጀመር አማራ ከብአዴን ጋር መቸ ነው አንድ ሆኖ የሚያውቀው??? ከጄኔራል አሳምነው ጽጌ ጋር አላግባባ ብሏቸው የቆየውስ ዋና ጉዳይ ምን ሆነና??? ትናንትናም ዛሬም የአማራ ቀንደኛ ጠላቱ ማን ሆነና???

እነኝሁ በአማራ ስም የሚነግዱ አስመሳይ የወያኔ ቅጥረኛ ግለሰቦችና ድርጅቶች የአማራን ወጣት ባጠቃላይም የአማራን ሕዝብ "ታገሱ ተረጋጉ ካልሆነ ሀገር ይፈርሳል!" የሚል ወያኔ "በሉ!" ያላቸውን ሲተፉብን በሚዲያ ተከታትላቹሃል፡፡ ቆይ አማራ "ሀገር ይፈርሳል!" እያለ ዘለዓለሙን በግፍ ሲቀጠቀጥና ሲደቆስ እንዲኖርና እንድናልቅ ነው ወይ የሚፈልጉት??? "ሀገር ይፈርሳል!" እያልን ሁሉንም የምንታገስ ከሆነ ወያኔና ሌሎች የጥፋት ኃይሎች ሳይሳቀቁ እንደፈለጉ እንዲያደርጉን፣ የፈለጉትን ዓይነት ግፍ እንዲፈጽሙብን ዋስትና እየሰጠናቸው እንደሆነስ ይገባቹሃል ወይ እነ ደናቁርት??? ለመሆኑ አሁን አፍን ሞልቶ ሀገሪቱ አልፈረሰችም ማለት ይቻላል ወይ??? ሀገር ሲፈርስ መሬቱ የሚደረማመስ ይመስላቹሃል እንዴ??? ከዚያ ውጭ በፈረሰ ሀገር የሚደርሰው ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ያልደረሰ ነገር አለ??? እናም አጋጣሚው በዚህ መልኩ በአማራ ስም የሚነግዱትን ቆሻሻ ቅጥረኞችን ማንነት ከመቸውም ጊዜ በላይ ግልጽ በማድረጉ፣

* ከሀገር ውስጥ በሳተላይት የሚተላለፉ ከአገዛዙ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የግል የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በሙሉ ኢንተርኔት በመቋረጡ ምክንያት ስርጭታቸውን ሲያቋርጡ ከአገዛዙና ከቅጥረኞቹ የሚወጡ ሐሰተኛ መረጃዎችን ለሕዝብ ያደርስ የነበረው ዐሥራት ቴሌቪዥን ግን የኢንተርኔት መቋረጡ እንቅፋት ሳይሆንበት ስርጭቱን ያቀርብ ነበር፡፡ ይሄም የሆነበት ምክንያት ዐሥራት ቴሌቪዥን የሚሠራው ለብአዴን/ወያኔ ስለሆነ አገዛዙ ለራሱ አገለግሎት ብቻ ክፍት ባደረገው የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲጠቀም በመደረጉ ነው፡፡

በኢንተርኔትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚሠራው ኔት ብሎክስ የተባለ ዓለም አቀፋዊ ድርጅት በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ 97% የኢንተርኔት አገልግሎት ሽፋን ተዘግቶ 3% ብቻ እየሠራ እንደሆነ ይፋ አድርጓል፡፡ ይህች ሦስት እጅም የተመረጡ የአገዛዙ ተቋማት ብቻ እንዲጠቀሙበት የተከፈተች ናት፡፡ ሌሎች ከሀገር ውስጥ የሚተላለፉ ከአገዛዙ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የግል የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በሙሉ በኢንተርኔት መቋረጥ ምክንያት ስርጭታቸውን ሲያቋርጡ ዐሥራት ቴሌቪዥን ከአገዛዙ የተመረጡ ተቋማትና በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሚቆጣጠራቸው የብዙኃን መገናኛዎች ጋር እንዲገለገል የተደረገው ማናችንም በግልጽ መረዳት እንደምንችለው ዐሥራት ቴሌቪዥን የሚሠራው ለብአዴን/ወያኔ በመሆኑና በካድሬዎቻቸው ቁጥጥር ስር ያለ በመሆኑ ነው፡፡ ወያኔ/ብአዴን እነኝህ ቅጥረኞቹ አብንና ዐሥራት ቴሌቪዥን እንዲህ ዓይነቱን ወራዳና የክህደት ሥራ ከሠሩ በኋላ በሕዝብ እንዳይጠረጠሩበትና እንዳይተፉበት ለማድረግ "ተሞክሮ የከሸፈ መፈንቅለ መንግሥት!" ከሚለው የፈጠራ ወንጀል ጋር በማያያዝ ከዐሥራት ቴሌቪዥን ሁለት ጋዜጠኞችን ሲያስር ከአብን ደግሞ ከሐምሳ በላይ ተራ አባላትን በአዲስ አበባና በተለያዩ ከተሞች እንዲታሰሩ አድርጓል፡፡

እነኝህ ለአማራ ክብርና ህልውና የተሠው ጀግኖቻችን እነ ጀኔራል አሳምነው ጽጌ በሠሩልን ጀብድ የአማራ ሕዝብ እነኝህ እነኝህን በስሙ የሚነግዱ ቅጥረኞችን ማንነታቸውን በሚገባ የመለየት ዕድል እንዲያገኝ አስችለውታልና ይሄም ጀግኖች አርበኞች ሠማዕቶቻችን ለአማራ ሕዝብ ያተረፉልን ተጨማሪ ድል ነው!!! መድኃኔዓለም ክርስቶስ የጀግኖች አርበኞች ሠማዕቶቻችንን ነፍስ ይማርልን አሜን!!!

ጽሑፉን በመጋራት ለሁሉም አድርሱ??? አመሰግናለሁ!

ድል ለአሳረኛው የአማራ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com